# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የትምህርት ሚኒስቴር



## የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን የደረጃ እድገት አፈጻጸም

## መመሪያ ቁጥር 1148/2018

ጳጉሜ /2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መመሪያ ቁጥር 1148/2018

## የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን የደረጃ እድገት አፈጻጸም መመሪያ

መምህራን ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት ብቃት ያላቸውና በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጹ ዜጎችን የማፍራት ታላቅ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ፤ መምህራን ይህንን አገራዊ ተልእኮ መወጣት እንዲችሉ በተለያዩ የሥልጠና ፕሮግራሞች የአቅም ግንባታ ሥርዓት እየተተገበረ የሚገኝ መሆኑ፤

በማስተማር ሥራቸው ውጤታማ የሆኑ መምህራንን ለማበረታታት፣ የሥራ ተነሳሽነታቸውን ለማሳደግ እና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ግልጽ የመምህራን የደረጃ እድገት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የደረጃ ዕድገት አተገባበሩ በአገሪቱ ከተደረገው የትምህርት ሥርዓት ለውጥ፣ ከመምህራን ሥልጠና ስትራቴጂዎች፣ እንዲሁም ከመምህራን የሥራ ምዘናና የደረጃ አወሳሰን ሥርዓት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

የትምህርት ሚኒስቴር በአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1368/2017 አንቀጽ 51(5) እና አንቀጽ 94(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርእስ**

ይህ መመሪያ "**የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን የደረጃ እድገት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር** 1148/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የኃረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "**ሚኒስቴር**" ወይም "**ሚኒስትር**" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

2/ "**መምህር**" ማለት በመምህርነት ሙያ ተመርቆ በማስተማር ሥራ ላይ የሚገኝ ባለሙያ ነው፤

3/ "**የትምህርት ተቋም**" ማለት በአጠቃላይ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1368/2017 ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕግጋት መሠረት ተመሥርቶ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጥበት ተቋም ነው፤

4/ "**የመምህራን የደረጃ እድገት**" ማለት በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተቀጥረው በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን በሥራ ቆይታ ዘመናቸው፣ በሥራ አፈጻጸም ውጤታቸውና በሌሎች መስፈርቶች እየተገመገሙ በደረጃ ዕድገት መሰላል ከአንድ ደረጃ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ የሚሸጋገሩበት ሥርዓት ነው፤

5/ "**የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ**" ማለት መምህራን በሥራ ላይ ሥልጠና የትምህርት ዝግጅታቸውን ከአንዱ ደረጃ ወደ ሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ ማሳደግ ነው፤

6/ "**ትይዩ የደረጃ እድገት**" ማለት መምህራን በሥራ ላይ ሥልጠና የትምህርት ደረጃቸውን ሲያሻሽሉ፣ ቀደም ብለው ይዘውት የነበረውን የደረጃ ዕድገት ማዕረግ እንደያዙ ላሻሻሉበት የትምህርት ደረጃ የተፈቀደውን ጥቅማጥቅም የሚያገኙበት ሥርዓት ነው፤

7/ "**ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ**" ማለት መምህራን በሥራ ላይ እያሉ ዕውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውን እና አመለካከታቸውን በየጊዜው በማደስ የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል የሚከውኑት ተግባር ነው፤

8/ **"ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ዕቅድ"** ማለት መምህራን በዓመቱ የትምህርት ቀናት በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ የሚያከናውኗቸውን ዝርዝር ተግባራት የሚያቅዱበት ሰነድ ነው፤

9/ **"ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሐ-ግብር"** ማለት መምህራን በሥራ ላይ እያሉ ዕውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውን እና አመለካከታቸውን በየጊዜው በማደስ የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል የተዘረጋ ሥርዓት ነው፤

10/**"የሙያ ትውውቅ"** ማለት አዲስ ወደ ሥራው የሚገቡ መምህራን ከትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ፣ ከሥርዓተ-ትምህርቱ እና ከሙያው ባሕሪ ጋር እንዲላመዱ የሚረዳ የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሐ-ግብር አካል ነው፤

11/**"የጉድኝት ማዕከል"** ማለት በአቅራቢያ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን በአንድ ማዕከል ሥር ሰብሰብ አድርጎ ማደራጀት ነው፤

12/**"ጽብረቃ"** ማለት መምህራን በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሐ-ግብር ያከናወኗቸውን ተግባራትና ያገኙትን ውጤት ለሌሎች መምህራን ወይም ለትምህርት ማኅበረሰቡ የሚያቀርቡበት አሠራር ነው፤

13/**"የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል"** ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ የመማር-ማስተማሩን ሂደት ለመደገፍ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚመረቱበትና የሚከማቹበት ቦታ ነው፤

14/**"ማኅደረ-ተግባር"** ማለት መምህራን በመማር-ማስተማር ሂደት ያከናወኗቸውን አንኳር ሙያዊ ተግባራት የሚያሳይ ሰነድ ነው፤

15/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴቶችንም ያጠቃልላል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በመምህርነት ሙያ ሰልጥነው በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቋሚነት ተቀጥረው በማስተማር ላይ በሚገኙ መምህራን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ በአፈጻጸማቸው ውጤታማ የሆኑ መምህራንን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የስራ ፍላጎትና ተነሳሽነት በማሳደግ የትምህርት ጥራትን ማሻሻል ነው።

# ክፍል ሁለት

# የደረጃ እድገት አፈጻጸም

## ንዑስ ክፍል አንድ

## የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን ሰባት የእድገት ደረጃዎች እና ማሟላት የሚገባቸው የጋራ መስፈርቶች

### 5. የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን የእድገት ደረጃዎች

የአጠቃላይ ትምህርት መመህራን የሚከተሉት ሰባት የእድገት ደረጃዎች አሉት፡-

| ተ.ቁ | የመምህራን ደረጃዎች ስያሜ | የቆይታ ግዜ |
|---|---|---|
| 1 | ጀማሪ መምህር | 0 ዓመት |
| 2 | መለስተኛ መምህር | 2 ዓመት |
| 3 | መምህር መምህር | 3 ዓመት |
| 4 | ከፍተኛ መምህር | 3 ዓመት |
| 5 | ተባባሪ መሪ መምህር | 3 ዓመት |
| 6 | መሪ መምህር | 3 ዓመት |
| 7 | ከፍተኛ መሪ መምህር | 3 ዓመት |

### 6. መምህራን የደረጃ እድገት ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው የጋራ መስፈርቶች

1/ ሁሉም በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን ለደረጃ ዕድገት ውድድር ሲቀርቡ፣ ለየደረጃው የተቀመጡ የመገምገሚያ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

2/ አንድ መምህር ከአንድ ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት፣ ወረዳ፣ ዞን ወይም ክልል/ከተማ አስተዳደር በሚዛወርበት ወቅት፤ የደረሰበትን የደረጃ እድገት መሰላል፣ የሚከፈለውን የደመወዝ መጠን፣ የደረጃ እድገቱን ያገኘበትን ቀን፣ ወርና ዓመት፣ የትምህርት ደረጃውን፣ እንዲሁም የደረጃ እድገቱን ካገኘ በኋላ የተሠራለትን የሥራ አፈጻጸም ውጤት በስንብት/በመሸኛ ደብዳቤው ላይ አስመዝግቦ ማቅረብ ይኖርበታል።

3/ ለሁሉም ደረጃዎች ለደረጃ እድገት የሚወዳደሩ መምህራን ለውድድር የሚቀርቡት ከዚህ በታች የተገለፁትን የጋራ መስፍርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡-

(ሀ) በመምህርነት የሙያ መስክ እውቅና ካለው ተቋም የተመረቀ እና በመምህርነት ሙያ ላይ በማገልገል ያለ፤

(ለ) የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ወይም አግባብ ባለው ሌላ መመሪያ በሚያዘው መሠረት ከባድ የዲስፕሊን የተቀጣ ከሆነ የተጣለበት የጊዜ ገደብ የተነሳለት፤

(ሐ) ከሚያስተምራቸው ተማሪዎች ውስጥ 75% እና በላይ የሚሆኑት 50% እና በላይ ማስመዝገባቸው ወይም ለደረጃው የተቀመጠውን ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ ማሟላታቸው በገለልተኛ አካል (በጉድኝት ማእከል፣ በወረዳ፣ዞን፣ በክልላዊ ወይም ሀገራዊ ምዘና) የተረጋገጠ፤

(መ) ለጀማሪ መምህራን የመውጫ ምዘና ያለፈ እና ለነባር መምህራን ደግሞ በሁሉም ደረጃ የሙያ ፈቃድ ምስክር ወረቀት መያዝ ይጠበቅባቸዋል፤

4/ ማንኛውም ጀማሪ መምህር ከመምህርነት የሙያ ትውውቅ በተጨማሪ በደረጃ እድገት የቆይታ ጊዜው ውስጥ በተለያዩ አካላት የሚሰጡ አጫጭር ሙያ ተኮር ስልጠናዎችን ቢያንስ ለ40 ሰዓታት ተከታትሎ ያጠናቀቀ መሆን አለበት፤

5/ ከመለስተኛ መምህር ደረጃ ጀምሮ ያሉ መምህራን ከተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ-ግብር በተጨማሪ፣ በደረጃ እድገት የቆይታ ጊዜያቸው ውስጥ በተለያዩ አካላት የሚሰጡ አጫጭር ሙያ ተኮር ስልጠናዎችን ቢያንስ ለ60 ሰዓታት ተከታትለው ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው፤

6/ በመንግስት የሚደረግ የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ መምህራን መደበኛ የደረጃ እድገት የሚያገኙበትን ጊዜ አያፋልስም።

7/ አንድ መምህር ከአንድ የደረጃ እድገት መሰላል ወደ ቀጣዩ የደረጃ እድገት መሰላል ማለፍ ካልቻለ ድጋሚ ለውድድር የሚቀርበው ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ ለሚወዳደርበት ደረጃ የሚጠይቀውን የቆይታ ጊዜና የደረጃ እድገት መወዳደሪያ መስፈርቶችን ሲያሟላ ይሆናል። በመምህራን የደረጃ እድገት ሥርዓት ውስጥ አንድ መምህር በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ለሁለት ጊዜ እድገት ማግኘት ባይችል ወይም ቢወድቅ ለሶስተኛ ጊዜ እንደገና የመወዳደር እድል አይኖረውም።

# ንዑስ ክፍል ሁለት

## የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን የደረጃ እድገት ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

7. **ጠቅላላ መስፈርቶች**

ሁሉም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ከጀማሪ መምህርነት እስከ ከፍተኛ መሪ መምህርነት ድረስ ባለው የደረጃ እድገት መሰላል ተጠቃሚ የሚሆኑት ሌሎች ከዚህ በታች በየደረጃው የተገለጹ መስፈርቶችን ማሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንግስት የትምህርት ተቋማት በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በመምህርነት ሙያ 10+3 ወይም 12+1 ወይም 12+2 ወይም 12+4 የሰለጠኑ ሲረጋገጥ ይሆናል።

8. **በጀማሪ መምህርነት ለመስራትየሚያስፈልግ መስፈርት**

በጀማሪ መምህርነት የሚመደብ መምህር ከመንግስት የትምህርት ተቋማት በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በመምህርነት ሙያ ሰልጥኖ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት።

9. **ከጀማሪ መምህርነት ወደ መለስተኛ መምህርነት ለማደግ የሚያስፈልግ መስፈርት**

በአንቀጽ 6 እና 7 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከጀማሪ መምህርነት ወደ መለስተኛ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በጀማሪ መምህርነት 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፣

2/ ጀማሪ መምህርነት ባገለገለባቸው የ2 ዓመታት (4 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 70 ከመቶ እና ከዛ በላይ ያገኘ፣

3/ የመምህርነት የሙያ ትውውቅ ለ2 ዓመት (4 ሴሚስተር) በአግባቡ ተከታትሎ ያጠናቀቀ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው።

10. **ከመለስተኛ መምህርነት ወደ መምህርነት ለማደግ የሚያስፈልግ መስፈርት**

በአንቀጽ 6 እና 7 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከመለስተኛ መምህርነት ወደ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በመለስተኛ መምህርነት 3 ዓመት እና ከዚ.ያ በላይ ያገለገለ፣

2/ በመለስተኛ መምህርነት ባገለገለባቸው 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 75 ከመቶ እና ከዚ.ያ በላይ ያስመዘገበ፤

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሀ ግብር እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባራቱ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው።

## 11. <u>ከመምህርነት ወደ ከፍተኛ መምህርነት ለማደግ የሚያስፈልግ መስፈርት</u>

በአንቀጽ 6 እና 7 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከመምህርነት ወደ ከፍተኛ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በመምህርነት ደረጃ ለ3 ዓመት ከዚ.ያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በመምህር ደረጃ ባገለገለባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 80 ከመቶ እና ከዚ.ያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባራቱ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ ብዛታቸው ከ2 ላለነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም ለደረጃ እድገቱ መሰላሉ ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደበ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

6/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ።

## 12. <u>ከከፍተኛ መምህርነት ወደ ተባባሪ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚያስፈልግ መስፈርት</u>

በአንቀጽ 6 እና 7 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከከፍተኛ መምህርነት ወደ ተባባሪ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በከፍተኛ መምህርነት ደረጃ ለ3 ዓመት እና ከዚ.ያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በከፍተኛ መምህርነት ደረጃ ባገለገሉባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 84 ከመቶ እና ከዛ በላይ እና ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባራቱ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደቡ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

6/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ፣

7/ በትምህርት ቤቱና በተማሪዎች የመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ አንድ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሄደ።

## 13. ከተባባሪ መሪ መምህርነት ወደ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚያስፈልግ መስፈርት

በአንቀጽ 6 እና 7 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከተባባሪ መሪ መምህርነት ወደ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በተባባሪ መሪ መምህርነት ደረጃ ለ3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በተባባሪ መሪ መምህርነት ደረጃ ባገለገሉባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 87 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባራቱ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣ ለትምህርት ቤቱ መምህራን ጽብረቃ ያደረገ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደቡ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

6/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ፣

7/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ አንድ ከዚያ በላይ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሄደና ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ።

## 14. ከመሪ መምህርነት ወደ ከፍተኛ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚያስፈልግ መስፈርት

በአንቀጽ 6 እና 7 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከመሪ መምህርነት ወደ ከፍተኛ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በመሪ መምህርነት ደረጃ ለ3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በመሪ መምህርነት ደረጃ ባገለገሉባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 90 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባራቱ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣ ለትምህርት ቤቱ መምህራን ጽብረቃ ያቀረበ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በትምህርት ክፍል ወይም በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ የትምህርት ቤት ኮሚቴዎች ውስጥ በኃላፊነት ወይም በአባልነት አንድ አመትና ከዚያ በላይ የሰራ፣

6/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደቡ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

7/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ፣

8/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ አንድና ከዚያ በላይ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሄደ፤ የጥናቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ፣ በውጤቱ ላይ ተመስርቶ የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጀና ከሚመለከተው ጋር በትብብር የተገበረ።

## ንዑስ ክፍል ሶስት
## ከአንደኛ ደረጃ (1ኛ-6ኛ) ትምህርት መምህራን የደረጃ እድገት ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

15. **ጠቅላላ መስፈርቶች**

ሁሉም የአንደኛ ደረጃ(ከ1ኛ-6ኛ) መምህራን ከጀማሪ መምህርነት እስከ ከፍተኛ መሪ መምህርነት ድረስ ባለው የደረጃ እድገት መሰላል ተጠቃሚ የሚሆኑት በየደረጃው ሌሎች ከዚህ በታች የተገለጹ መስፈርቶችን ማሟላት ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንግስት የትምህርት ተቋማት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት በመምህርነት ሙያ 10+3 ወይም 12+1 ወይም 12+2 ወይም 12+4 የሰለጠኑ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

## 16. <u>በጀማሪ መምህርነት የሚመደብ መምህር</u>

በጀማሪ መምህርነት የሚመደብ መምህር ከመንግስት የትምህርት ተቋማት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት በመምህርነት ሙያ ሰልጥኖ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት።

## 17. <u>ከጀማሪ መምህርነት ወደ መለስተኛ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 8 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከጀማሪ መምህርነት ወደ መለስተኛ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በጀማሪ መምህርነት 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፣

2/ በጀማሪ መምህርነት ባገለገሉባቸው 2 ዓመታት (ለ4 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 70 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የመምህርነት ሙያ ትውውቅ ለ2 አመታት (ለ4 ሴሚስተር ) በአግባቡ ተከታትሎ ያጠናቀቀ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው።

## 18. <u>ከመለስተኛ መምህርነት ወደ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 8 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከመለስተኛ መምህርነት ወደ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በመለስተኛ መምህርነት 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በመለስተኛ መምህርነት ባገለገሉባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 75 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባራቱ ላይየተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በትምህርት ቤቱ በተቋቋሙ ክበባት ወይም ኮሚቴዎች ቢያንስ በአንዱ የተሳተፈ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ አንድ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሄደ።

## 19. <u>ከመምህርነት ወደ ከፍተኛ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 8 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከመምህርነት ወደ ከፍተኛ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በመምህርነት ደረጃ 3 ዓመት ከዚያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በመምህርነት ባገለገለባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሰሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 80 ከመቶ እና ከዚ.ያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙ.ያ ማሻሻ.ያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባሩ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊ.ያ ማዕከል ወይም በትምህርት ክፍል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ ኮሚቴዎች በኃላፊነት ወይም በአባልነት ከአንድ ዓመት ያላነሰ የሰራ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ አንድ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሄደና ጥናቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ፤

7/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም ለደረጃ በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደቡ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

8/ ለሚያስተምረው የትምህርት ደረጃ የተዘጋጀውን የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ የገመገመ እና የግምገማውን ውጤት አጠናቅሮ ለሚመለከተው አካል ያስረከበ፤

9/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ።

## 20. <u>ከከፍተኛ መምህርነት ወደ ተባባሪ መሪ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 8 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከከፍተኛ መምህርነት ወደ ተባባሪ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በከፍተኛ መምህርነት 3 ዓመት እና ከዚ.ያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በከፍተኛ መምህር ባገለገለባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 84 ከመቶ እና ከዚ.ያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙ.ያ ማሻሻ.ያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባሩ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣ ለትምህርት ቤቱ መምህራን ጽብረቃ ያደረገ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በትምህርት ክፍል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ ኮሚቴዎች በኃላፊነት ወይም በአባልነት ከአንድ ዓመት ያላነሰ የሰራ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ አንድ እና ከዚያ በላይ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሄደና ጥናቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ፣

8/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደቡ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

9/ ለሚያስተምረው የትምህርት ደረጃ የተዘጋጀውን የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ የገመገመ እና የግምገማውን ውጤት አጠናቅሮ ለሚመለከተው አካል ያስረከበ፤

10/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ።

## 21. <u>ከተባባሪ መሪ መምህርነት ወደ መሪ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 8 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከተባባሪ መሪ መምህርነት ወደ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በተባባሪ መሪ መምህርነት 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በተባባሪ መሪ መምህርነት ባገለገለባቸው ተከታታይ የ3 ዓመት (የ6 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 87 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባሩ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣ ለትምህርት ቤቱ መምህራን ጽብረቃ ያደረገ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በትምህርት ክፍል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ ኮሚቴዎች በኃላፊነት ወይም አባልነት ከአንድ ዓመት ያላነሰ የሰራ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ ሁለት ተግባራዊ ጥናትና ምርምሮችን ያካሄደና ጥናቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ፣

7/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደቡ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

8/ ለሚያስተምረው የትምህርት ደረጃ የተዘጋጀውን የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ የገመገመ እና የግምገማውን ውጤት አጠናቅረው ለሚመለከተው አካል ያስረከበ፤

9/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ፣

10/ ለሚያስተምረው የትምህርት ዓይነት ለማጣቀሻነት የሚያገለግል አጋዥ ጽሑፍ ለተማሪዎች ያዘጋጀ፣

11/ አዳዲስ አሰራሮችን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ሌሎች ለመማር ማስተማር ስራ የሚያግዙ ስራዎቸን ያከናወነ።

## 22. <u>ከመሪ መምህርነት ወደ ከፍተኛ መሪ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 8 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከመሪ መምህርነት ወደ ከፍተኛ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በመሪ መምህርነት ለ3 ዓመት እና በላይ ያገለገለ፤

2/ በመሪ መምህርነት ባገለገሉባቸው ተከታታይ 3 ዓመት (6 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 90 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባራቱ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፤ ለትምህርት ቤቱ መምህራን ጽብረቃ ያደረገ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በትምህርት ክፍል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ ኮሚቴዎች በኃላፊነት ወይም በአባልነት ከአንድ ዓመት ያላነሰ የሰራ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ ሁለት እና ከዚያ በላይ ተግባራዊ ጥናትና ምርምሮችን ያካሄደና ጥናቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ፤

7/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደቡ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

8/ በሚያስተምረው የትምህርት አይነት የተዘጋጀውን የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ የገመገመ እና የግምገማውን ውጤት አጠናቅሮ ለሚመለከተው አካል ያስረከበ፤

9/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ፣

10/ በሚያስተምረው የትምህርት ዓይነት ለተማሪዎች ማጣቀሻነት የሚያገለግል አጋዥ ጽሑፍ ያዘጋጀ፣

11/ በሌሎች መምህራን በተዘጋጀ ትምህርታዊ ጽሑፎች ወይም ጥናቶች ወይም መሰል ሥራዎች ግምገማ ላይ የተሳተፈ፣

12/ የማሰልጠኛ ጽሑፍ በማዘጋጀት ለትምህርት ቤቱ መምህራን ስልጠና የሰጠ፤

13/ አዳዲስ አሰራሮችን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ሌሎች ለመማር ማስተማር ስራ የሚያግዙ ስራዎቸን ያከናወነ።

## ንዑስ ክፍል አራት

## <u>መካከለኛ (ከ7ኛ-8ኛ) እና ሁለተኛ ደረጃ (ከ9ኛ-12ኛ) ትምህርት መምህራን የደረጃ እድገት ለማግኘት የሚጠበቁ መስፈርቶች</u>

### 23. <u>አጠቃላይ መስፈርት</u>

የመካከለኛ (7-8) እና የሁለተኛ ደረጃ (9-12) መምህራን ከጀማሪ መምህርነት እስከ ከፍተኛ መሪ መምህርነት ባለው የደረጃ እድገት ተጠቃሚ የሚሆኑት ሌሎች በየደረጃው የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንግስት የትምህርት ተቋማት ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት በመምህርነት ሙያ 10+3 ወይም 12+2 ወይም 12+4 እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመምህርነት ሙያ 12+3 ወይም 12+4 የመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል።

### 24. <u>በጀማሪ መምህርነት የሚመደብ መምህር</u>

በጀማሪ መምህርነት በመካከለኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት የሚመደብ መምህር ከመንግስት ትምህርት ተቋማት ለእርከኑ በተዘጋጀው የመምህርነት ሙያ ስልጠና ወስዶ የምስክር ወረቀት ያለው መሆን አለበት።

### 25. <u>ከጀማሪ መምህር ወደ መለስተኛ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 9 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከጀማሪ መምህርነት ወደ መለስተኛ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በጀማሪ መምህርነት 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፣

2/ በጀማሪ መምህርነት ባገለገሉባቸው 2 ዓመታት (4 ሴሚስተር) አማካይ የስራ አፈጻጸም 70 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የመምህርነት የሙያ ትውውቅ ለ2 አመታት (ለ4 ሴሜስተር) ተከታትሎ ያጠናቀቀ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው።

26. <u>ከመለስተኛ መምህርነት ወደ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 9 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከመለስተኛ መምህርነት ወደ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በመለስተኛ መምህርነት 3 ዓመት ከዚያ በላይ ያገለገለ፣

2/ በመለስተኛ መምህርነት ባገለገለባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የሥራ አፈጻጸም ውጤቱ 75 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባራቱ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በትምህርት ክፍል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ ኮሚቴዎች በኃላፊነት ወይም በአባልነት ቢያንስ ከአንድ ዓመት ያላነሰ የሰራ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ አንድ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሄደ፤

7/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ።

27. <u>ከመምህርነት ወደ ከፍተኛ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 9 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከመምህርነት ወደ ከፍተኛ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በመምህርነት ደረጃ 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፣

2/ በመምህርነት ደረጃ ባገለገሉባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የሥራ አፈጻጸም ውጤት 80 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባሩ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በትምህርት ክፍል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ ኮሚቴዎች በኃላፊነት ወይም በአባልነት ቢያንስ ከአንድ ዓመት ያላነሰ የሰራ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ አንድ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሄደና ጥናቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ፤

7/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ፣

8/ ለሚያተምረው ትምህርት የተዘጋጀውን የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መማሪያ መጻህፍ የገመገመ እና የግምገማውን ውጤት አጠናቅሮ ለሚመለከተው አካል ያስረከበ፤

9/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመጡ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

10/ በሌሎች መምህራን በተዘጋጁ ትምህርታዊ ጽሑፎች ወይም ጥናቶች ወይም መሰል ሥራዎች ግምገማ ላይ የተሳተፈ።

## 28. ከከፍተኛ መምህርነት ወደ ተባባሪ መሪ መምህርነት ለማደግ

በአንቀጽ 6 እና 9 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከከፍተኛ መምህርነት ወደ ተባባሪ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በከፍተኛ መምህርነት ደረጃ 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በከፍተኛ መምህርነት ደረጃ ባገለገሉባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የሥራ አፈጻጸም ውጤት 84 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባሩ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፤ ለትምህርት ቤቱ መምህራን ጽብረቃ ያደረገ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በትምህርት ክፍል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ ኮሚቴዎች በኃላፊነት ወይም በአባልነት ከአንድ አመት ያላነሰ የሰራ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ አንድ እና በላይ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሄደና ጥናቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ፤

7/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ፣

8/ በሚያስተምረው የትምህርት አይነት የተዘጋጀውን የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ የገመገመ፤ የማሻሻያ ሀሳብ ያቀረበ እና አጠናቅሮ ለሚመለከተው አካል ያስረከበ፤

9/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመጡ እጩ መምህራን አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

10/ በሚያስተምረው የትምህርት ዓይነት ለተማሪዎች ማጣቀሻነት የሚያገለግል አጋዥ ጽሑፍ ያዘጋጀ፣

11/ በሌሎች መምህራን በተዘጋጁ ትምህርታዊ ጽሑፎች ወይም ጥናቶች ወይም መሰል ሥራዎች ግምገማ ላይ የተሳተፈ፣

12/ አዳዲስ አሰራሮችን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ሌሎች ለመማር ማስተማር ስራ የሚያግዙ ስራዎችን ያከናወነ።

## 29. <u>ከተባባሪ መሪ መምህርነት ወደ መሪ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 9 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከተባባሪ መሪ መምህርነት ወደ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በተባባሪ መሪ መምህርነት 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በተባባሪ መሪ መምህርነት ደረጃ ባገለገሉባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የሥራ አፈጻጸም ውጤት 87 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግባሩ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣ ለትምህርት ቤቱ መምህራን ጽብረቃ ያደረገ፣

4/ በአግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በትምህርት ክፍል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ ኮሚቴዎች በኃላፊነት ወይም በአባልነት ከአንድ ዓመት ያላነሰ የሰራ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ ሁለት ተግባራዊ ጥናትና ምርምሮችን ያካሄደና ጥናቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ፤

7/ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን፣ ሴት፣ ወይም ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕፃናትን በመለየት ድጋፍና አገልግሎት የሰጠ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ ያደረገ፣

8/ በሚያስተምረው የትምህርት አይነት የተዘጋጀውን የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ የገመገመ፤ የማሻሻያ ሀሳብ ያቀረበ እና አጠናቅሮ ለሚመለከተው አካል ያስረከበ፤

9/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በደረጃ እድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደቡ እጩ መምህራን ቢያንሰስ አንድ አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

10. በሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት ለተማሪዎች ማጣቀሻነት የሚያገለግል አጋዥ ጽሑፍ ያዘጋጀ፣

11. በሌሎች መምህራን በተዘጋጁ ትምህርታዊ ጽሑፎች ወይም ጥናቶች ወይም መሰል ሥራዎች ግምገማ ላይ የተሳተፈ፣

12. አዳዲስ አሰራሮችን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ሌሎች ለመማር ማስተማር ስራ የሚያግዙ ስራዎቸን ያከናወነ ነው።

## 30. <u>ከመሪ መምህርነት ወደ ከፍተኛ መሪ መምህርነት ለማደግ</u>

በአንቀጽ 6 እና 9 የተጠቀሱ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከመሪ መምህርነት ወደ ከፍተኛ መሪ መምህርነት ለማደግ የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1/ በመሪ መምህርነት 3 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፤

2/ በመሪ መምህርነት ደረጃ ባገለገሉባቸው ተከታታይ 3 ዓመታት (6 ሴሚስተር) አማካይ የሥራ አፈጻጸም ውጤት 90 ከመቶ እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

3/ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ እቅድ በማዘጋጀት ለ3 ተከታታይ ዓመታት በተግበሩ ላይ የተሳተፈና በአግባቡ የፈጸመ፣ ለትምህርት ቤቱ መምህራን ጽብረቃ ያደረገና የተሰጠውን ግብረ መልስ ተግባራዊ ያደረገ፣

4/ አግባቡ የተደራጀ ማህደረ ተግባር ያለው፣

5/ በዩኒት መሪነት ወይም በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም በትምህርት ክፍል ወይም በክበባት ወይም በተለያዩ ኮሚቴዎች በኃላፊነት ወይም በአባልነት ከአንድ ዓመት ያላነሰ የሰራ፣

6/ በመማር ማስተማር ችግሮች ዙሪያ ሶስት ተግባራዊ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂደና ጥናቱን ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለውይይት ያቀረበ፤

7/ ልዩ ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች ወይም ሴት ተማሪዎችን ወይም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችንና ሕጻናትን በመለየት ድጋፍ የሰጠ፣ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደረገ፣

8/ በሚያስተምረው የትምህርት አይነት የተዘጋጀውን የመምህሩን መምሪያና የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ የገመገመ፤ የማሻሻያ ሀሳብ ያቀረበ እና አጠናቅሮ ለሚመለከተው አካል ያስረከበ፤

9/ ብዛታቸው ከ2 ላላነሱ ጀማሪ መምህራን ወይም በእድገት መሰላል ከራሱ በታች ለሆኑ መምህራን ወይም ለተግባር ልምምድ ከመምህራን ስልጠና ተቋማት ለሚመደቡ እጩ መምህራን ቢያንስ አንድና አመትና በላይ በአማካሪነት ተመድቦ የሰራ፣

10/ በሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት ለተማሪዎች ማጣቀሻነት የሚያገለግል አጋዥ ጽሑፍ ያዘጋጀ፣

12/ የማሰልጠኛ ጽሑፍ በማዘጋጀት ለትምህርት ቤቱ መምህራን ስልጠና የሰጠ፤

13/ በሌሎች መምህራን በተዘጋጁ ትምህርታዊ ጽሑፎች ወይም ጥናቶች ወይም መሰል ሥራዎች ግምገማ ላይ የተሳተፈ፣

14/ አዳዲስ አሰራሮችን፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ሌሎች ለመማር ማስተማር ስራ የሚያግዙ ስራዎቸን ያከናወነ።

## ክፍል ሦስት

## የመምህራን የትምህርት ደረጃ ማሻሻያና የትይዩ የደረጃ እድገት አፈጻጸም

### 31. በመንግሥት ትምህርት ተቋማት የትምህርት ደረጃቸውን በመንግሥት ወጪ በስራ ላይ ስልጠና ያሻሻሉ መምህራን

1/ መምህራን በማስተማር ስራ ላይ ሆነው ለመምህራን ስልጠና በተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት መሰረት የትምህርት ደረጃቸውን ሲያሻሽሉ ቀደም ሲል ይዘውት የነበረውን የደረጃ እድገት እንደያዙ የሚቀጥሉ ሆኖ የትምህርት ደረጃቸውን ባሻሻሉበት ደረጃ የተቀመጠውን የደመወዝ መጠን በትይዩ የሚያዝላቸው ይሆናል፤

2/ ለመምህራን ስልጠና በተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት በማስተማር ላይ ሆነው ትምህርታቸውን ተከታትለው የትምህርት ደረጃቸውን አሻሽለው ማስረጃ ሲያቅርቡ ትምህርት ላይ የቆዩበት ጊዜ ለደረጃ እድገት የሚቆጠርላቸው ይሆናል፤

3/ ለመምህራን ስልጠና በተዘጋጀው ሥርዓት ትምህርት በመደበኛ መርሀ ግብር ከማስተማር ስራ ውጭ ሆነው የትምህርት ደረጃቸውን አሻሽለው ማስረጃ ለሚያቀርቡ መምህራን ትምህርት ላይ የቆዩበት ጊዜ ለደረጃ እድገት አይቆጠርም። ነገር ግን የትይዩ የደረጃ እድገት የሚሰራላቸው ወደ ትምህርት ተቋም ከመሄዳቸው በፊት በነበሩበት የደረጃ እድገት መሰላል መሰረት ይሆናል፤

4/ የትምህርት ደረጃቸውን አሻሽለው የትምህርት ማስረጃ የሚያቀርቡ መምህራን ትይዩ የደረጃ እድገት የሚያዝላቸው ከተመረቁበት ቀን ጀምሮ ሲሆን የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉ መምህራንም የትምህርት ማስረጃቸውን እስከ 3 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣ ከ3 ወር በላይ በራሳቸው ምክንያት ዘግይተው ካቀረቡ የትምህርት ማስረጃው የሚያዝላቸው ካመለከቱበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣

5/ በመንግስት ዕቅድ የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉ መምህራን የትምህርት ማሻሻያው ሲያዝላቸው በሰለጠኑበት የትምህርት አይነት ባሉበት ትምህርት ቤት ወይም በሌሎች የመምህር እጥረት ባለባቸው ትምህርት ቤቶች ተመድበው የመሥራት ግዴታ አለባቸው፣

6/ የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ የሚያዝላቸው መምህራን የደረጃውን መነሻ ደመወዝ ደርሰውበት ወይም አልፈውት ከሆነ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

32. <u>በመንግሥት የትምህርት ተቋማት በመምህርነት ሙያ በግላቸው በስራ ላይ ስልጠና የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉ መምህራን</u>

በሥራ ላይ ያሉ መምህራን በግላቸው ትምህርት ሚኒስቴር ባዘጋጀው የመምህራን ማሰልጠኛ ስርዓተ ትምህርት መሰረት ሰልጥነው የትምህርት ደረጃቸውን ሲያሻሽሉና የተማሩት የትምህርት መስክ ከሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፣ ክፍት ቦታና በጀት መኖሩ ተረጋግጦ የትምህርት ደረጃ ማሻሻያው ተይዞላቸው ከተመደቡበት ቀን ጀምሮ የትይዩ የደረጃ እድገት ተጠቃሚ ይሆናሉ። ነገር ግን የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉ መምህራን ብዛት ካለው ክፍት ቦታ በላይ ከሆነ ምደባው በውድድር የሚፈጸም ይሆናል።

## ክፍል አራት

## የተፋጠነ የደረጃ እድገት አሰጣጥ

33. **የላቀ አፈጻጸም ላስመዘገቡ መምህራን የተፋጠነ ደረጃ እድገት የሚሰጥበት ሁኔታ**

1/ ከመምህርነት እስከ መሪ መምህርነት የደረጃ እድገት መሰላል ያለ አንድ መምህር በሚያስተምረው ትምህርት አይነት ሁሉንም ተማሪዎች ውጤት 85% እና ከዚያ በላይ በተከታታይ ሁለት አመታት እንዲያስመዘግቡ ካደረገ እና ይህም በገለልተኛ አካል ደረጃውን የጠበቀ ምዘና ለተማሪዎች በመስጠት ሲረጋገጥ ለደረጃ እድገቱ የሚጠይቀውን የሶስት ዓመት የቆይታ ጊዜ ሳይጠብቅ በሁለት ዓመት ውስጥ ወደ ሚቀጥለው የደረጃ እድገት መሰላል እንዲሸጋገር ይደረጋል።

2/ ከመምህርነት እስከ መሪ መምህርነት የደረጃ እድገት መሰላል ያለ አንድ መምህር በሚያስተምረው ትምህርት ሁሉንም ተማሪዎች ውጤት 90% እና ከዚያ በላይ በተከታታይ ሶስት አመታት እንዲያስመዘግቡ ካደረገ እና ይህም በገለልተኛ አካል ደረጃውን የጠበቀ ምዘና ለተማሪዎች በመስጠት ሲረጋገጥ መምህሩ አንድ የደረጃ እድገት መሰላል እዲዘል በማድረግ ወደሚቀጥለው የደረጃ እድገት እንዲሸጋገር ይደረጋል። ሆኖም ከፍተኛ መሪ መምህርነት የደረጃ እድገት ላይ ያለ መምህር በሚያስተምረው ትምህርት ሁሉንም ተማሪዎች ውጤት 90% እና ከዚያ በላይ በተከታታይ ሁለት አመታት እንዲያስመዘግቡ ካደረገ እና ይህም በገለልተኛ አካል ደረጃውን የጠበቀ ምዘና ለተማሪዎች በመስጠት ሲረጋገጥ መምህሩ ሁለት የእርከን ጭማሪ እንዲያገኝ ይደረጋል።

34. **በልዩ ሁኔታ የደረጃ እድገት አፈጻጸም**

1/ መምህራን በደረሱበት ደረጃ እድገት መሰላል 2 ዓመትና በላይ በማስተማር ሥራ ላይ አገልግለው ወደ ሌላ የሥራ መደብ ተዛውረው ከሰሩ በኋላ 2 አመት ሳይሞላቸው ወደ መምህርነት ሲመለሱ በተጨማሪ ለ1 ዓመት በመምህርነት አገልግለው ቀደምሲል የነበራቸው አገልግሎት ተይዞላቸው የ6 ጊዜ (ስድስት ሴሚስተር) ግምገማቸው ታይቶ ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት ሲያሟሉ ቀደመው ከነበሩበት ቀጥሎ ያለውን የደረጃ እድገት መሰላል እንዲያገኙ ይደረጋል።

2/ አንድ መምህር በደረሰበት የጤና ችግር ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ከማስተማር ሥራ እንዲገለል በመንግስት ሆስፒታል በሐኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ መሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ

ሆኖ ባገኘው ቦታ በጊዜያዊነት መድቦ የሚያሰራው ከሆነና መምህሩም በተመደበበት ጊዜያዊ ቦታ ላይ አጥጋቢ ውጤት ካስመዘገበ ከማስተማር ሥራ በተገለለበት ጊዜ ከነበረበት ቀጥሎ ወደ አለው የደረጃ እድገት መሰላል ለአንድ ጊዜ ብቻ ለውድድር ሊቀርብ ይችላል። ሆኖም መምህሩ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ከህመሙ አገግሞ ወደ ማስተማር ሥራው ሊመለስ ካልቻለ በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ መሠረት ወደ ሌላ የሥራ ዘርፍ ተዛውሮ እንዲሰራ ይደረጋል።

3/ አንድ መምህር በደረሰበት የጤና ችግር ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ከማስተማር ሥራ እንዲገለል በመንግስት ሆስፒታል በሐኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ የደረጃ እድገት የሚያገኝበት ጊዜ ከደረሰ ከመታመሙ በፊት በነበረው የስራ አፈጻጸም ውጤት ወይም በተመደበበት የስራ ዘርፍ አፈጻጸሙን በመገምገም ለአንድ ጊዜ ብቻ ለደረጃ እድገት ውድድር የሚቀርብ ይሆናል።

4/ በደረጃ እድገት ኮሚቴ ስህተት ምክንያት ደረጃ እደገት ያላገኘ መምህር የተፈጠረው ስህተት እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ከታወቀ የደረጃ እድገት ማግኘት ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ተጠቃሚ ይሆናል። ሆኖም ከስድስት ወር በኋላ ችግሩ ከታወቀ በቀጣዩ የደረጃ እድገት የውድድር ጊዜ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል። በዚህ ምክንያት የደረጃ እድገት ጊዜው የሚዛባበት መምህር ቀጣዩን የደረጃ እድገት የሚያገኘው በደረጃ እድገት ኮሚቴው በስህተት የታለፈውን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ ይሆናል።

5/ ሴት መምህርት በወሊድ ፈቃድ ላይ እያለች የደረጃ እድገት የምታገኝበት ጊዜ ከደረሰ ከወሊድ በፊት በነበራት የሥራ አፈጻጸም ውጤት መሰረት ለደረጃ እድገት ውድድር የምትቀርብ ይሆናል።

6/ በትምህርት ደረጃ ማሻሻያ የሚገኝ ትይዩ እድገትና በቆይታ ጊዜ የሚገኝ የደረጃ እድገት በአንድ ጊዜ ሲመጡ መምህሩ በሁለቱም ተጠቃሚ ይሆናል።

7/ በየደረጃው በሚገኙ የመምህራን ማህበር ጽሕፈት ቤቶች በሙሉ ጊዜ አመራርነት የሚያገለግል ማንኛውም መምህር የደረጃ እድገት ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆነው ለማህበሩ አመራሮች ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ በሚውለው የመገምገሚያ መስፈርት መሠረት ይሆናል።

8./ በተመላላሽነት በአመራርነት የሚያገለግሉ መምህራን የሥራ አፈጻጸም ምዘና 40% ለማህበሩ አመራሮች በተዘጋጀው የመገምገሚያ መስፈርት እና 60% በትምህርት ቤት ደረጃ ለመምህራን በተዘጋጀው የመገምገሚያ መስፈርት መሠረት ተገምግመው፣ ውጤቱ ወደ 100% በመቀየር ተፈጻሚ ይደረጋል።

35. <u>የመምህራን የደረጃ እድገት የሚያገኙበት ጊዜ</u>

1/ ከጥር 1 እስከ ሰኔ 30 ባለው ጊዜ የተቀጠሩ መምህራን የደረጃ እድገት የሚያገኙት ከሀምሌ 1 ጀምሮ ይሆናል፡፡

2/ ከሐምሌ 1 እስከ ታህሳስ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ የተቀጠሩ መምህራን የደረጃ እድገት የሚያገኙት ከጥር 1 ጀምሮ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የደረጃ እድገት ኮሚቴ አደረጃጀት እና ተግባርና ኃላፊነት</u>

36. <u>የትምህርት ቤት ደረጃ እድገት ኮሚቴ አደረጃጀት</u>

1. የትምህርት ቤት የደረጃ እድገት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

(ሀ) የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ------------------------------------------ሰብሳቢ

(ለ) የትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር ወይም ተወካይ ---------------- አባልና ፀሐፊ

(ሐ) የመሠረታዊ መምህራን ማኅበር 2( አንድ ሴት ተወካይ) ተወካይ---------አባል

(መ) በእጩነት የሚቀርበው መምህር የሚገኝበት የትምህርት ክፍል ኃላፊ ----- አባል

2. የደረጃ እድገት ስራው ሰብሳቢን እና ጸሐፊ ጨምሮ በአብላጫ የኮሚቴ አባላት በተገኙበት ይከናወናል፡፡

37. <u>የትምህርት ቤት የደረጃ እድገት ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ ከትምህርት ቤቱ የደረጃ እድገት ቴክኒክ ኮሚቴ ተጣርቶ የቀረበለትን የመምህራንን መረጃ ፈትሾ ለደረጃ እድገት ውድድር የሚቀርቡ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

2/ የትምህርት ቤቱን መምህራን የደረጃ እድገት ይሰራል፡፡

3/ በትምህርት ቤት ደረጃ የጋራ ውሳኔ የተደረሰበትን የመምህራንን የደረጃ እድገት ለወረዳው ትምህርት ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፡፡

38. <u>የትምህርት ቤት የደረጃ እድገት ቴክኒክ ኮሚቴ አደረጃጀት</u>

1/ የትምህርት ቤት የደረጃ እድገት ቴክኒክ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለትምህርት ቤቱ ደረጃ እድገት ኮሚቴ ሲሆን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

(ሀ) የትምህርት ቤቱ ምክትል ርዕሰ መምህር ወይም ተወካይ----------------------ሰብሰቢ

(ለ) ከትምህርት ክፍል ኃላፊዎች በመምህራን የሚወከሉ 2------------------አባልና ጸሐፊ

(ሐ) መሰረታዊ መምህራን ማኅበር 2 ተወካይ (አንዱ ሴት ተወካይ) -----------አባል

2/ የደረጃድገት ፋይል የማጣራትና የማረጋገጥ ስራ የኮሚቴው ሰብሳቢን እና ጸሐፊ ጨምሮ በአብላጫ የኮሚቴ አባላት በተገኙበት እንዲሰራ ይደረጋል።

39. <u>የትምህርት ቤት የደረጃ እድገት ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባር እና ኃላፊነት</u>

1/ ለደረጃ እድገት የሚወዳደሩ መምህራንን ፋይል ከሚመለከተው ክፍል በመረከብ በትክክል ለውድድር የሚቀርቡ ስለመሆናቸው ያጣራል፣

2/ በትምህርት ቤት ለደረጃ እድገት ውድድር የሚቀርቡ መምህራንን ይለያል፣

3/ የተጣራውን ፋይልና ቃለጉባኤ በማደራጀት ለትምህርት ቤቱ የደረጃ እድገት ኮሚቴ ያስረክባል፣

4/ ለውድድር የተለዩ መምህራን ስም ዝርዝር በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አማካይነት ግልጽ በሆነ ቦታ እንዲለጠፍ በማድረግ መምህራን እንዲያውቁት ያደርጋል፣

40. <u>የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ሀላፊነት</u>

ከትምህርት ቤቱ የቀረበለትን የደረጃ እድገት የሚያገኙ መምህራን ትክክለኛነት አረጋግጦ ያጸድቃል።

41. <u>የጥቅም ግጭት እና የአሰራር ስርዓት</u>

1/ የጥቅም ግጭት ማለት አንድ የኮሚቴ አባል በኮሚቴው ውስጥ የሚያከናውነው ተግባር ወይም የሚሰጠው ውሳኔ ከራሱ ወይም ከቤተሰቡ የግል ጥቅም፣ ዝምድና ወይም ሌላ ቀጥተኛ ግንኙነት ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ እና በገለልተኝነት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ሁኔታ ነው።

2/ ማንኛውም የኮሚቴ አባል ተግባሩን እና ኃላፊነቱን ሲወጣ ፍጹም በሆነ ገለልተኝነት፣ በታማኝነት እና ፍትሃዊነት የመስራት ግዴታ አለበት።

3/ የመምህራን የደረጃ እድገት አፈጻጸም በሚከናወንበት ወቅት፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተጠቀሰው ዓይነት የጥቅም ግጭት መኖሩን የተገነዘበ ማንኛውም የኮሚቴ አባል፤ ስራው ከመጀመሩ በፊት የጥቅም ግጭት መኖሩን ለኮሚቴው በይፋ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

4/ የጥቅም ግጭት መኖሩ በኮሚቴው ሲረጋገጥ፣ ጥቅሙ የሚነካው አባል በጉዳዩ ላይ በሚደረግ ማንኛውም ውይይት ወይም ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ በከፊል ወይም በሙሉ እንዳይሳተፍ ኮሚቴው ውሳኔ ያስተላልፋል።

5/ ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ፣ አንድ የኮሚቴ አባል ገለልተኛ ሳይሆን ውሳኔ ሰጥቷል ብሎ ካመነ፣ ጉዳዩን ለሚመለከተው ተገቢ አካል አቤቱታ የማቅረብ እና አባሉ ከሂደቱ እንዲገለል የመጠየቅ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

42. <u>የቅሬታ አቀራረብ</u>

መምህራን በደረጃ እድገት አፈፃፀም ላይ ቅሬታ ሲኖራቸው የደረጃ እድገት ደብዳቤ በእጃቸው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታቸውን ለወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ያቀርባሉ። ሆኖም ቅሬታ አቅራቢዎች በሚሰጣቸው ምላሽ የማይረኩ ከሆነ የሲቪል ሰርቪስ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርአትን ተከትለው ቅሬታቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ።

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

43. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ትብብር የተጠየቀ አካል የመተባበር ግዴታ አለበት።

44. <u>ተጠያቂነት</u>

ይህን መመሪያ ተፈፃሚ ያላደረገ ወይም መመሪያውን ተላልፎ የተገኘ አካል አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

45. <u>ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጎች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

46. <u>መመሪያን ስለማሻሻል</u>

እንደ አስፈላጊነቱ መመሪያውን የማሻሻል ስራ የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊነት ይሆናል።

47. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ**

**ጳጉሜ 2018 ዓ.ም**

**ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**